# “የሌባ ዓይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ”

## ግልጽ ደብዳቤ ለዶ/ር ጌታቸው በጋሻውና መሰሎቹ!

*በቅርቡ “ የተቃዋሚ ተቃዋሚን ታጋይ ጀግኖች” በሚል ርዕስ ጉልላት በሚል የብዕር ስም (በዶ/ር ጌታቸው በጋሻው) ለተጻፈ የስድብ ውርጂብኝና ብዙ የሚያጠያይቅ ክስ ይዞ ብቅ ላለ ጽሁፍ የተሰጠ ምላሽ።*

ከላይ የጠቀስኩት ጽሁፍ ባለቤት ዶ/ር ጌታቸው መሆኑን ካረጋገጥሁ በኋላና የጽሁፉን ይዘት ከስድቡ ውርጅብኝ ባሻገር በጥንቃቄ ስመለከተው በጣም ያሳዘነኝ ከ25 ዓመት በፊት በሱዳን ምድር ከትግሉ ሜዳ በውሃ ቀጠነ በትነውን ለስደተኝነት የዳረጉን ግለሰቦች እነማን እንደሆኑ እየታወቀ ያለፈው አለፈ ፣ ለትግሉ መስዋዕት አድርገናቸው የመጣነው ወገኖች ዛሬ አደብ ተገዝቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃ የሚያወጣና የስልጣኑ ባለቤት ሊያደርጉት የሚያስችሉ ግለ ሰቦችን ሁሉ የኋላ ታሪካቸውን መመልከቱ አያሻም ብለን ያኔ ያደረጉትን ብተና እንዳላየን ሆነን ስንተያይ እንደማያቅ ሰላምታ ሳንነፍጋቸው ኑረን ዛሬ ዶ/ር ጌታቸው በዚህ ጽሁፉ እጣቱን ቀስሮ የነበረውን ድክመት በአንድ ግለ ሠብ ላይ ለመላከክ ሲውተረተር ስታዘብ አይ እንግዲህስ ይብቃ! ይብቃ! ውሸቱ ያቁም! በማለት ነው ይህንን ምላሽ እንድሰጥ የተገደድኩትኝ።

በመጀመሪያ ለዶ/ር ጌታቸውም ሆነ ለመሰሎቹ ላሳስብ የምፈልገው ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ሕዝብ በደም በአጥንቱ የገነባው የትግል ሀውልቱ እንጂ የዶ/ር ጌታቸውና የጓደኞቹ ወይም የእያሱ ወይም ዛሬ በድርጅቱ ውስጥ ያሉና የሌሉ ብቻም አይደለም።የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረትነቱ የተረጋገጠ ስለሆነም ማንም አገር ወዳድ ይህ የድርጅት ሃውልት እንዳይፈርስ የመከላከል ግዳታው ነው የሚል ጽኑ ዕምነት አለኝ። ለዚህም ነው ሕዝቡ በአብዛኛው አንድ ኢትዮጵያ! አንድ ኢሕአፓ! አንድ ቅንጅት! እያለ ተለጣፊነትን የሚኮንነው። ይህንን ደግሞ እነ ዶ/ር ጌታቸው ጠፍቷቸው አይደለም።

ሌላው ደግሞ ዶ/ር ጌታቸውና መሰሎቹ እንዲረዱት የምፈልገው ላለፉት ሠላሣ እና አርባ ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ባደረገው ትንንቅ ውስጥ ለተሠሩ ስህተቶች ማንም እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንጹህ ነኝ ብሎ እጁን ሊታጠብ አይችልም። ዛሬ በኢሕአፓ ውስጥ ኖርንም አልኖርንም ወይም ሰልፋችን ከሌላ ሆነ ተብሎ ያኔ ተሠሩ ለሚባሉ ስሕተቶች ሁሉ ጥቂት ግለሰቦችን ተጠያቂ ማድረግ ዕብደት ይመስለኛል። ይልቁንስ እያንዳንዳችን በነቂስ ተጠያቂነታችንን መገንዘብ ትልቅ ዕውቀት ነው። ስለ ስህተት ሲወራ ደግሞ ልንመለከተው የሚገባ ነገር ቢኖር ማን ከሕዝቡ ወገን ሆኖ ስህተት ሠራ ማን ደግሞ ሕዝቡን ለማስጎንበስ ውይም ለግል ዕውቅናና ሌላም ሌላ መናኛ ተልካሻ ምክንያትና ክህደት እጁን በደም አጠበ ነው። ይህንን ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመናገር ነፃነቱ ሲከበር ዕውነታውን ታሪክ እንደሚናገር አልጠራጠርም።

እንደ እኔ ዓይነቱን ዝም ለማሰኘት “ጉልላት” በሚል ስም ተሰድቤአለሁ እያሉ እነ ዶ/ር አሥሩን ቢቀባጥሩ ዕውነትና ንጋት እያደር ይጠራል እንደሚሉ ባለፉት አራት ወራት ውስጥ ብቻ ማን አፍራሻ ኃይል ማን ደግሞ ከሕዝቡ ወገን እንደሆነ ቁልጭ ብሎ እየታየኝ እንዲመጣ ዶ/ሩና ጓደኞችህ በተግባር ለእንደኔ ያለው በማያጠራጥር ሁኔታ እንዳረጋገጣችሁ ልገልጽ እወዳለሁ። ምናልባትም ዛሬ በኢሕአፓ ላይ ያደረግኸውን ሕገ-ወጥ መሠሪ ሥራህን ለመሸፈን ስትል ከዚህ በፊት ስለተደረጉት ብተናዎችም ጭምር ሳትፈራ የባጥ የቆጡን ስትመትር በቂ ማስረጃ እየሰጠኸኝ ስለሆነ ዛሬ የደረስኩበት ድምደማ ላይ እንድደርስ ገፍተህ አድርሰኸኛል። እንግዲህ ከዚህ በታች አቶ ጉልላት (ዶ/ር ጌታቸው) በየድሕረ-ገጹ ባዳረስከው መጣጥፍ ላይ አለፍ አለፍ ብዬ እያጣቀስኩ እነሆ ትዝብቴን ላስቀምጥልህ፦

**አቶ ጉልላት ጽሁፉን እንዲህ ሲል ይጀምራል፦**

> *"መቸም ትውልዱ ያልታደለ ፤ አገሪቱም ከቴውድሮስ እና ከበላይ ዘለቀ ወንድ ልጅ አይወለድብሽ እርግማን,,,,,"* ብሎ በመቀጠል *" እኛ ያልመራነው ህብረትና ግምባር ብትንትኑ ይውጣ ፤ ወዘተ-- ወዘተ-- በማለት በመሳሪያ ጠላትን አርበድብዶ በረሃውን በጅግንነት አስጨንቆ የወገን ጥብቅናን ከማስከበር ይስቅ በፖለቲካ የላቀውን ፤ በትግል ስልት የቀደመውን ፤ በፖለቲካ አመለካከቱ የተለየውን ፤ በሳይበር ጦርነት አልሞ ለመተኮስ----"* ይልና ለጠቅ አድርጎ ደግሞ

> *" በተለይም አሁን ከውስጣቸው ተለይቶ የወጣው ኢሕኢፓ ዲሚክራሲያዊ በከፈተው የመነጋገሪያ ፎረም በመስተንግዶው በልዩነት አብሮ መስራትን እንዴት በአጭር ጊዜ ውስጥ በተግባር ለማሳየት እየሞከረ እንደሆነ መረዳት ያቃታቸው እነ ነገር ቁርሱ የሸሙጥ ብዕር ትራሱ እያሱ አለማየሁና የትግል ሞራላቸው ከውስጣቸው ለአንዴም ለመጨረሻም ተመልሶ ላይጎበኛቸው የተሰናበታቸው ቡችሎቹ ቃል የተጋቡ የሚመስሉት በድሕረ-ገጽ ደብተራውን በፓልቶክ ደግሞ አሲምባን እና የኢቲዮጵያውያን ፎረምን በነገር መኸገርነት----እነ አቶ እያሱና የቢራ ጠርሙስ ጨብጠው በመነጋገሪያ ሳይበርና በድሕረ-ገጽ በብተና የሚከሷቸው እንደሚያወሩት ወንጀለኞች ነበሩ?"*

**ዶ/ር ጌታቸው (ጉልላት) ፤ የብዕር ስምህ ብቻ ብዙ ይናገራል። አየህ እነ ቴዎድሮስና በላይ ዘለቀ ያንን ጥቅስ ቢያጣቅሱ በጊዜው ታሪክ የጣለባቸውን ኃላፊነት በመወጣት ታሪክን ሰርተው ምስዋዕትነትን በመቀበል እንጂ በሸሸትና ሌባ ጣታቸውን በሌላ ወገናቸው ላይ ለመጠቆም እንዳልሆነ የታወቀ ነው። ዶ/ሬ አንተና ግብረ-አበሮችህ ተስማምታችሁ ከጓዶቻችሁ ጋር የድርጅታችሁ የበላይ አካል የሆነው ጉባኤ ላይ ተቀምጣችሁ ገና ሳይጀመር በጠፍ ጨረቃ ጥላችሁ ወጥታችሁ ሕገ-ወጥነትን እየደለቃችሁ ያዙኝ ልቀቁኙ ምን የሚሉት ነው? ዶ/ር ጌታቸው አፄ ቴዎድሮስ ወይም በላይ ዘለቀ እንደ አንተንና መሰሎችህ በዚያ ጉባኤ ተሳትፈው ቢሆን ኖሮ እንዲያው የከፋ ነገር እንኳ ቢመጣ ከዚያ አዳራሽ ሬሳቸው ተጎትቶ ይወጣ እንደሁ እንጂ የመጡበትን ታሪክ ሠርተው ሰሚም ቢያጡ ፀሐይ ሞቋቸው ሰው አይቶአቸው ይሄዱ ነበር እንጂ የበሉበትንና የከረሙበትን የሆቴል ሂሳብ እንኳ ሳያወራርዱ ሸሽተው በውርደት ይሄዱ ይመስልሃል? (በነገራችን ላይ እናንተ ያደረጋችሁትን የማይደግፉ አባላት በዚያ አስቸኳይ ጉባኤ ላይ ለመገኘት ለሄዳችሁት ሁሉ እንዲሆን ከየአካባቢው ለአዘጋጅ ኮሚቴው የተላከ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ገንዘብ ያንተው ቡድን ይዞ መፈርጠጡን የሚያረጋግጡ የተሰረዙ ቼኮች ግልባጭ ወሬውን ሰምቼ አላምንም ብዬ ግልባጩን እንዳየው ብቻ ተልኮልኝ በእጄ ላይ እንዳለ ላሳስብህ እፈልጋለሁ)።**

**ለአንባብያንም የዚህ ጽሑፌ ርዕስ ያደረግኩትን ለመጠቀም ካስገደደኝ ምክንያቶች አንዱ ከዚህ በላይ የጠቀስኩት የሂሳብ ማወራረድ ጉዳይ እንደሆነ እንድትገነዘቡልኝ ምናልባትም የመረጥኩት ርዕስ ካልጣማችሁ ትልቅ ይቅርታ እጠይቃለሁ።**

**በነገራችን ላይ ፖለቲከኞቻችን ሥልጣን ሳይዙ የሚያሳዩት ግድፈትና ወራዳ ባሕርያት ስልጣን ቢይዙ እጥፍ ድርብ ሆኖ በአምባገነንነት ሊተረጎም እንደሚችል ጠንቅቀን ማወቁና በተለይም ወያኔን እንታገላለን ስላሉን ብቻ አጸያፊውን ባሕርያቸውን ሁሉ ማስተናገድ እንደሌለብንና የፖለቲካችንን ደረጃ ከፍ የማድረግ ኃላፊነቱ ፤ ብሎም ፖለቲከኞቻችን የጨዋታውን ሕግጋት ማክበር ግዴታቸው እንደሆነ የማስገንዘቡና ነውሩን ነውር ማለቱ ወደኋላ ያለማለት የእያንዳንዱ ሀገር ወዳድ ኃላፊነት መሆኑን ላሰምርበት እፈልጋለሁ።**

እንግዲህ ዶ/ር ጌታቸው መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች የሚያነሱ ወገኖች ራሳችንን ሳንሱር እንድናደርግ ፤ እናንተ ፖለቲከኞች የሀገራችንና የወገኖቻችንን ጥቅም በሃራጅ ስትቸረችሩ ተማልካች ወይም ደጋፊ ካልሆንን የቢራ ጠርሙስ ጨብጠን የምንምበዛበዝ አድርገህ ስትገልጸን (ማስረጃው ካለህና ዕውነትም ከሆነ እኛስ የቢራ ጠርሙስ ብንጨብጥ ሰርቀን ያመጣነው ስላልሆነ አናፍርበትም) ለመሆኑ አንተና መሰሎችህ ስዬ አብርሃ ምኑን አስጨብጧችሁ ነው "በልዩነት አብሮ መሥራትን በአጭር ጊዜ ውስጥ በተግባር ባሳያችሁበት" መድረካችሁ ስዬን ስለ ፀጋዬ ደብተራው በአሁኑ ጊዜ መጠየቅ ትክክል አይደለም ስትሉን የከረማችሁት? ኸረ ለመሆኑ እናንተ እነ ማናችሁና ምንስ ጨብጣችሁ ነው ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ዕምነት አጉድላችሁ በዘረፋችሁት የኢሕአፖ ንብረት በሆነው በወሺንግተን ዲሲ የሚገኝ የኅብረት ራዲዮ ጣቢያ ለስዬ አብራሃ ስብሰባ ተገኙለት ስትሉ የከረማችሁት? እነስዬ አብራሃና ግብረ አበሮቹ ተቃዋሚዎቻቸውን ኢህአፓዎችንም ጨምሮ በቁም በአደባባይ በዕሳት ያጋይዋቸው እንደነበር ታውቃላችሁ? (የሰበሰብናቸውን መረጃዎች በአሲምባ ድሕረ-ገጽ ላይ ሂዱና አድምጡ)። ስዬ ዛሬ በጥቅም ተጣልቶ ኢ-ፍትሃዊ ድርጊት ቢደርስበትም ለሕዝባችን ባጠመደው ወጥመድ መሰሎኝ የተያዘው? ለመሆኑ ለሠራው በደልስ በአደባባይ ይቅርታ ጠይቋል? ለምንስ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ከ"በልዩነት አብሮ መሥራት" ጠበላችሁ አታካፍሉትም? የኦነግንና የሌሎች ድርጅት መሪዎችን በመድረካችሁ ስትጠሩ ላለማችሁት የስም ማጥፋት እንዲተባበሯችሁ ኢሕአፓን እንዲኮንኑላችሁ አመቻችታችሁ ላቀረባችኋቸው ጥያቄዎች እንኳ ፍንጭ ሳይሰጧችሁ ፤ ሳይረዷችሁ የሄዱበትን መድረክ ነው "በልዩነት አብሮ መሥራት" የሚባልልን። አይ ጉድ! ማፈሪያዎች ናችሁ!

ዶ/ር ጌታቸው አንድ ነገር ላስታውስህ ፤ በአሲምባ ያለን መድረኩን የምናንቀሳቅስ ወገኖች የማንም ቡችሎች አለመሆናችንን ያረጋገጥነው ገና በጧቱ ከሁለት ዓመት በፊት የኢሕአፓ አመራሮች ነን እናነጋግራችሁ ብላችሁ (ዛሬ አንጃኞች ሆናችሁ የወጣችሁት አመራር አባላት በጊዜው እንደተነገረን በማዋቀር ስም መድረኩን በቁጥጥር ሥር ለማዋል ስታነጣጥሩ ፤ አሁን ግን ሁሉም ካለፈ በኋላ ግልጽ ሆኖአል) ግርግር የፈጠራችሁ ጊዜ ነው። ያኔ ደግሞ እያሱ አላነጋገረንም። በጊዜው አመራሩን ወክለን መጥተናል ላሉትም ምን ዓይነት መልስ እንደሰጠን ለምን እነፀጋዬን አትጠይቅም። ከእኛም ጋር አብረውን ይሠሩ የነበሩቱ (አሉላና ሻዓብ)እኮ አጠገብህ አሉልህ እነሱም አሠራራችንን ፤ ማንም የሚያሾረን አለመሆናችንና በቅንነት በራሣችን አነሳሽነት የዚያን ትውልድ ታሪክ ሳይበረዝና ሳይደለዝ ለማስቀመጥ የተነሳሳን ወገኖች መሆናችንን ያውቁታልና ባልፈሱበት አያፍሩበትም ነው ነገሩ። እንግዲህ የኢሕአፓ አመራር ማለት ለእኛ በጊዜው እነእያሱንም ስለሚጨምር የተሰጣቸው መልስ ለጠቅላላው ኢሕአፓ የነበረና የማንንም ተፅዕኖ እንደማንቀበል ቆፍጠን ያለ በቴሌፎን በኮንፈረንስ ስብሰባ በተሳተፍነው ሁሉ ተመዝግቦ የተቀመጠ ስለሆነ ጭራውን የሚቆላልህ ውሻ የማያውቁህ ሀገር ሂድና ፈልግ ነው መልሱ!

ሌላው ደግሞ በኅብረት አብሮ መሥራት ማለት መተክልን መሸጥ ካልሆነ በስተቀር እስከዛሬ ለፈረሱ የኅብረት እንቅስቃሴዎች ፤ኢሕአፓን ፤ መኮንን ከሁሉም በላይ ደግሞ ህለህብረቶች መመሥረትና መጠንከር ከፍተኛ ድርሻ ያበረከተን ድርጅት እንደአፍራሽ መፈረጅ ትልቅ አላዋቂነትና ችግሮችም በቅጡ እንዳይመረመሩ አንገቷን ከአሸዋ የምትቀብረውን ሰጎን መሆን እንጂ አርቆ አስተወይነት ከሚጠበቅበት መሪ ያውም ዶ/ር ነኝ ባይ ስሰማ ምን ያህል ክስረትና ማደናገር እየተካሄደ እንደሆነ በቁጭት ልገነዘብ ችዬአለሁ። ይልቁንም እያንዳንዱ መሪ ነኝ ባይ በጠቀስካቸው የሕብረት እንቅስቃሴዎች ያለፈ ሁሉ ለደረሱት ውድቀቶች ተጠያቂ ነው እላለሁ። ያ ደግሞ እያሱን ብቻ ሳይሆን አንተንም ይጨምራልና እየተስተዋለ። እንዲያው ለሁሉም ውድቀት እያሱና ፋሲካ ላይ መላከክ ወይ እነዚህ ወገኖች የሌላቸውን መለኮታዊ ያፍዝ ያደንግዝ ኃይል መስጠት አለያም የማደናቆርያ ውሸት ፋፋ ሲነሰነስብን አዙረን ነገሮችን የምናጤን ወገኖች እንደሌለን የሚያስቂጥር አባዜ የተጠናወታችሁ የሕዝብ ንቀትና ትዕቢት የወጠራችሁ መሆኑን ያሳየኛል። ገና ለገናም ከታሪክ ትፋቶች ድጋፍ እናገኛለን ብላችሁ ከዚህ በፊት "ቀዩ መስመር እንዳይጣስ" ብለን በአሲምባ ያለን ወገኖቻችሁ እንዳላሳሰብናችሁ ሁሉ ዴሞክራሲያዊ ኢሕኢፓዎች ነን ብላችሁ ካልጋ ወደ አልጋ ብትዘሉ እኮ ፤ በየሄዳችሁበት ሁሉ በከረንት አፌር እንኳ ሳይቀር ስማችሁን ቀይሩና ማንነታችሁን ክዳችሁ ኑና አስመስክሩ ነው የተባላችሁት። እናንተም አላፈራችሁም ፤ በዚህ አላቆማችሁም። ኢሕአፓ ድርጅቶችን እየከፋፈለ ነው እያላችሁ ቅንጅትን እንደምሳሌ በሰጣችሁ ማግስት ፕሮፌሰር

መስፍን በቅንጅት ውስጥ የነበረውን ቅራኔ ገና ከጽንሱ እንደነበረ መስክረው አሳፈሯችሁ። ከኢሕአፓ ውስጥ ተገንጥላችሁ ከወጣችሁ ጀምሮ የኢሕአፓን ክፉ ነገር እያነፈነፋችሁ ዋናው ትግላችሁ ከወያኔ ጋር ከመሆን ይልቅ እናድነዋለን ከምትሉት ከኢሕአፓ ጋር ሆኖ ፤ ግና እስክስታ ስትወርዱ የማየው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ጋር ለመሆኑ ብዥታ የለኝምና ታዲያ የተቃዋሚውን ተቃዋሚ የታጋይ ሃፍረቶቹ ዶ/ር ጌታቸው የምትመራው አንጃና አንተን አምነው የሚከተሉህ ሁሉ ለመሆናችሁ ለእኔ ከመቼውም ቂዜ ግልጽ ሆኖ ኮለል ብሎ እየጠራ መምጣቱን እሳካሁን ላለፉት አራት ወራት በቡድን እየሠራችሁ ያላችሁት በበቂ አሳይቶኛል። ይህንንም ስድብ ካላችሁት ግንባራችሁ ላይ ለጥፋችሁ ዙሩ።

ዶ/ር ጌታቸው (ጉልላት) ሌላው በዚህ ፅሁፍሕ በጣም ያንገበገበኝና ያሳዘነኝን ደግሞ ላቅርብና የሚሰማኝን ልናገር፡-

“ *በ1972 ዓ/ም ግንቦት ወር መጨረሻ ክልል 2 ወይም (Region 2) በመባል ይታወቅ በነበረው አካባቢ እንንቀሳቀስ የነበርን የሠራዊቱና የፓርቲ አባላት ፓርቲውን ለማዳን ሽንፋ ከተባለ ወንዝ ላይ ስብሰባ በተቀመጥንበት ወቅት እነ ደሳለኝን (ዶ/ር ጌታቸው) ተራ አባላት በጥያቄ ስናዋክባቸው አቶ እያሱ አሊ ከሚባል ድርጅቱ ለተለየ ሙያ ገዳሪፍ አስቀምጦት በነበረው ግለሰብ የሞቀ ቤት ውስጥ እየተንፈላሰሱ አልነበረምን?*

*ምነው ወደ ሽንፋ በረሃ በመምጣትስ እኛ ጋር ተቀምጠው በመምከር ድርጅቱ ከመበተን አደጋ ለማትረፍ ያልሞከሩት ፤ገዳሪፍ ላይ ተኮፍሰው የማንን ጎፈሬ እያበጠሩ ነበር? ከሽንፋው ስብሰባ ተሰፋችን ተሟጦ ወደ ቲሃ እንደገባንስ እነ ኮረኔል አስናቀ እንግዳ መሳሪያውን ለአገር ወዳድ ታጋዮች ይሰጥ ብለው ሲደራደሩን ተጠይቀው ጆሮ ዳባ ልበስ አላሉምን?----*” ብሎ ይቀጥላል።

ዶ/ር ጌታቸው ዛሬም እንደምትነግረን ያኔም ፓርቲውን የማዳን ታሪካዊ ኃላፊነት ተጣለብኝ ትላለህ? እኸሳ አዳንከው? የማውቀው በዚያን ጊዜ ብተና መካሄዱን ነው። ያንን ኃላፊነቱን በእያሱ ለመላከክ ስትረረጥ ሳይ ደግሞ ግርም ይለኛል። የያኔውንም በአንድ ግለ ሠብ ላይ አሁንም የሌባ ጣትህን በዚሁ ታነጣጥራለኸ። እኔስ ዕድሜህን በሙሉ ስትታገል የነበረው እያሱን ነው ብዬ ታዝቤሃለሁ። አንድ ሌባ ጣትህን በአንድ ግለሰብ ላይ አነጣጥረህ መአት ልታወራ በምትሞክርበት ጊዜ ሌሎቹ ዘጠኙ ወደራስህ ላይ እያመለከቱ አንተው ባንተው እየተሳለቀብህ ጀምበር እየመሸ መሆኑን አትርሳው።

ሌላው ደግሞ በኢሕአፓ በኢሕአሠ ውስጥ የነበረው ኃይል በአብዛኛው እያንዳንዱ በነቂስ መሪ መሆን የሚችል ከጦር አበጋዝነት እስከ መምህራን የሠራተኞች መሪዎች ወጣቶች ሴቶች ገበሬዎች የነበሩበት ትልቅ ድርጅት ነበር። በዚያው በሜዳ እንኳ ካስተማርናቸው ገበሬዎች መሪነታቸውን በተግባር በመስዋዕትነት የከፈሉ የማከብራቸው ዛሬም በኅይወት ያሉ አያሌ ወገኖች ያሉበት ድርጅት ሆኖ ሳለ ታዲያ ካንተ በላይ ሌላ ለድርጅቱ የሚያስብ ሰው እንዳልነበረ አድርገህ ስታቀርብ ግርም ነው ያለኝ። አንተ እንዳስቀመጥከው በጊዜው የፓርቲው አንዱ የበላይ አካል ሆነህ እያሱ በሱዳን ገዳሪፍ ተኮፍሶ ካስቸገረህ በጊዜው የበላይ የፓርቲው ልዑክነትህና ያንን የሸንፋ ስብሰባ ከሚመሩት መካከል እንደመሆንህ መጠን ለምንድርነው ሠራዊቱን በጊዜው መሪነት ስጥተህ ትግሉን ከማስቀጠል ይልቅ ጦር መሳሪያ ተቀብሮ ከሱዳን ምድር እንዲገባና ያ ያልከው ችግር እንዲደርስበት ያስደረግኸው? በአሁኑ ወቅት ሀገራችን ላለችበት ቀውስ የ30 ዓመቱን ታሪክ ማንሳቱ በወያኔ ላይ እንዳናተኩር እጃችን እንዲዝል ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር ጥቅሙ አይታየኝም ፤ ግና ካነሳኸው አይቀር ፤ እንዲያው እንነጋረርበት ከተባለ ፤ ካጠገብህስ በሸንፋ ስብሰባ ሲካሄድ ክፍሉ ታደሰ የኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል አልነበረም እንዴ? እንደአፄ ቴውድሮስ ታሪክ የመሥራቱ ዕድል እኮ በሰፊው ነበረላችሁ። ተጋዳዩ መቼም አልታገልም ብሎ ሱዳን ወይም ሞት ብሎ አላመጸ! በዚህ በጻፍከው ጽሁፍ መሣሪያውም የተወሰደበትን ምክንያት ሳይቀር በእያሱ ላይ ልታደርግ እየዳዳህ ትመስላለህ። በነገራችን ላይ ስሙን የጠቀስከው ፀጋዬ ደብተራው አንተ ወደ አሜሪካን ከመጣህ በኋላ ለብዙ ዓመታት ፍንክች ሳይል እስከተያዘበት ጊዜ ትግሉን እንዳስቀጠለ የሚታወቅ ነው። መሪነትም ታሪክን መሥራትም ይሉሃል ይህን ይመስላል። በእኔ እምነት ያ ትኩስ ኃይል ተበትኖ እንዲቀር ካደረጉት የወቅቱ መሪዎች አንዱ በታሪክ ከመጠየቅ የማትድን ለመሆንህ አትጠራጠር። እንዲያው ሆድ ይፍጀው ብለን የተውነውን ነገር እየቆሰቆስክ ብዙ መላልሰህ አትጉዳን። እኔስ ይብላኝላቸው ዛሬም ለሚከተሉህ!

ለማጠቃለል፦

በሀገራችን ዴሞክራሲያዊና የሕግ የበላይነት የሚሰፍንበት ሥርዓት ለመመሥረት እየታገልን ባለንበትም በአሁኑ ጊዜ ፤ የሚያታግሉን ድርጅቶች በውስጣዊ አሠራራቸውም ሆነ ከሕብረተ-ሰቡና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ያላቸው ግንኙነት የሕግ የበላይነት መኖሩን የሚያረጋግጥ አሠራርና ምሥፈርት ሊኖራቸው ይገባል። ዛሬ በትግል ውስጥ ስላለን እንደፈለግነው የድርጅት ደንቦችን እየጣስን በሕብረተሰቡም ውስጥ ልንፈረጅ የምንችልበትን ደረጃዎች ዝቅ አድርገን ሥርዓት አልበኝነትን የምንቀፈቅፍ ከሆነ ነገ ወያኔን የምንተካው ለሕግ በማይገዙ ሌሎች አምባገነኖች ሊሆን እንደሚችል እያንዳንዳችን ልንረዳ ይገባል። ድሮ በብር የላስቲክ ኳስ መንደራችን ውስጥ ስንራገጥ እንኳ የአፍሪካን ዋንጫ የሚያጫውቱት ዳኞች ያክል የጨዋታ ህግ ባናስከብርም ፣ ልንከተለው የሚገባ የጨዋታ ሕግጋት ነበሩን። አንዳንዴ ጉልበተኞች ላለመሸነፍ ወይም ደግሞ ኳሳችንን ቀምተው ሊሮጡ ሲያምራቸው የጨዋታውን ህግ እየጣሱ ግብ ሊያስቆጥሩ የሞክሩ ጊዜ የጨዋታ ፍርሻ ይሆን ነበር። እንዲያም ሲል መፋጠጥ እስከመደባደብ ይደረስ ነበር።

በሀገራችን የፖለቲካ መስክ ዕውቀቱ ሳያንሳቸው ሕገ-ወጥነትን የሚያራምዱ በእኔ ዕምነት ዋነኛ አጀንዳቸው በሕዝቡ የሞቀ ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ለማፍሰስ የሚፍጨረጨሩ ባለ ልዩ ተልዕኮዎች ናቸውና ነቅተን ልንጠብቀቸውና ልናጋልጣቸው ይገባል እላለሁ።

ዛሬ ያለንበት ወቅት ለሚቀጥለው ትውልድ ለግተን ልናስተላልፈው የማንችል ሀገራችንን ከጥፋት የማዳን ርብርቦሽ በማድረግ ፤ ኢትዮጵያዊነትን ከዘረኞች መንጋ ለመከላከል የአንድነት ኃይሎችን አሰባስቦ የኃይል ሚዛን በመለወጥ የተሰረቀውን የሕዝብ ድምፅ ለማስመለስ የሞት የሽረት ትንንቅ የምናደርግበት ጊዜ እንጂ አንተና መሰሎችህ ቀኝ ሲሏችሁ ግራ ፤ በውሃ ቀጠነ ድርጅት ማፍረስ ፤ "በታማኝ ተቃዋሚ" ስም ሽብረክረክ! ወያኔ ራሱ ያወጣውን ስሙን "ወያኔ አንበለው!" ብሎ አካኪ ዘራፍ ፤ አንዴ ደግሞ "ጥፋተኞች ነን ብለን ፊርመን ወያኔ ሕጋዊነት ካልሰጠን መታገል አይቻልም" በማለት ሕዝቡ አጥብቆ እንዳይታገል ጨለምተኝነትን ማስፋፋት ፤ ልክ እነ ወያኔ ሕጋዊ ሆነው ታግለው ከዚህ የደረሱ ይመስል! ትግል አልጋ ባልጋ ይመስል የታጋይነት ቅስም እየሰበራችሁ ፤ በአይናችን የምንመሰክረውን እንኳ ሕጋዊ ሆነው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችና ግለ-ሰቦች በቅርብ ተለጣፊ ካልሆኑ እያደማቸው እንደሆነ የምትክዱ! ኸረ ስንቱ!

አንገብጋቢው ጥያቄ ሕጋዊ የመሆን ወይም አለመሆን ፤ ትግሉ ሰላማዊ የመሆን ወይም ያለመሆን አይደለም። በየትኛውም ቦታ በማንኛውም ዓይነት ኢትዮጵያዊነትን ለማስከበር ፤ ለፍትህ ለዴሞክራሲ ፍንክች አለማለትን ፤ ከብረት የጠነከረ ዕምነትን ይዞ ሕዝቡን አስተባብሮ መሪነትን ሰጥቶ አይቀሬ መስወዕትነትን ከፍሎ ግዳጅን መወጣት ነው! ወያኔ ያልሆነውን ቅብ ለመስጠት ወይም ደግሞ ከሌለበት ባሕርይ ዴሚክራሲ ሊያመጣ እንደሚችል አድርጎ ለማቅረብ መዳዳት እነታምራት ለይኔ ያሉበትን መርሳት ፤ ከታሪክ አለመማር ወይም በሬ ሆይ በሬ ሆይ ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ አይነት ሆዳምነት ነው።

ስለዚህ ከሺህ ዶ/ር ጌታቸው በጋሻዎች "በታማኝ ተቃዋሚ" ስም የሚያታገሉ ቆራጥ ድርጅቶችን የሚያፈርሱ ፤ የቆራጥ አታጋዮችን ስም የሚያጠፉ ፤ የመንደር ሰንበቴ ማህበር እንኳ ሲመሠርቱ ታይተው የማይታወቁ ልፍስፍሶች አንድ እያሱ አንድ ፋሲካ ባመኑበት ጸንተው የኖሩ ፤ እንደእስስት ሳይገለባበጡ ፍንክች ሳይሉ ዕድሜአቸውን የገፉ ለኔስ አምባገነኖቹ ይሻሉኛል። አሁንም ከሺስ ዶ/ሮች የባለብዙ መቶ ገጽ መጽሐፍ ጻፍን ዕውቀተ ብዙዎች ፤ "የሰለጠኑ ፖለቲከኞች" ፤ታሥሬአለሁና ጉሮ ወሸባዬ በሉልኝ ፤ የመጽሐፍ ሽፋናቸው ግን ወያኔና ሻቢያ በጠመንጃ ኃይል ያዋቀሩትን የኢትዮጵያ ካርታ ከፍ አድርጎ የሚያሳይ ፤ ወይም ሕዝቡ ያልተቀበለውን አስቀድሞ ተምሬአለሁ ባዩ ተሸናፊነትን ያንፀባረቀበትንና አዲሱ ትውልድ ስለኢትዮጵያዊነት ያለው ስነልቡናዊ ዕውቀቱን በተዘዋዋሪ መንገድ እየሰለቡ ለመሆናቸው የማይታያቸው! ሀገር ወዳዶችን አንኳሳሾች ፤ ለኦነጎችና ለሶማሌ ነጻ አውጭ ኢትዮጵያዊ አይደለንም ባዮች ሳይፈሩን በዓለም መድረክ መስካሪዎች ፤ ወይም ደግሞ ተመራጮች ነበርን ብለው ታሥረው እንኳ በያደባባዩ የጮኽንላቸው ተረስቶ ፤ አሜሪካን ሀገር ለዚያ ዳሃ ህዝብ የሚያስብ ኢትዮጵያዊ የሌለ ይመስል ሳያፍሩን ፤ ዓይን በዓይን ውሻ ለበላበት ይጮኻል እንዲሉ ዕድሉን አግኝተው እንኳን በዓለም አደባባይ ቢወጡ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ እስረኞች 100 ብቻ ናቸው ብለው ለወያኔ በሃሰት ከመሰከሩቱ ፤

ለኔስ አሁንም አንድ ሀገር ወዳድ ዶ/ር ታዬ ፤ አንድ ቃሌን አላጥፍም ባይ ኢንጂኔር ኃይሉ ሻውል ፤ ትምክኽተኛም ይበሉት ወይም ፊውዳል ይሻለኛል።

ይህንንም የምለው ታሪክ ሠሪነታቸውን ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሳይከዱ በተግባር ፤ በከፈሉት መስወዕት ስላረጋገጡልኝ ነው። ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው አንተስ የምትታገለው ወያኔን ወይስ ታጋዮችን? ሰልፍህስ ከየት ነው? ኢትዮጵያዊነት ወይም ሞት ብሎ መስዋዕትነትን በማስተማር ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን? ወይስ ተልመጥምጦ የጎጠኞች ጫማ ስሞ ተለጣፊ መሆንና ለኢትዮጵያዊነት መጥፋት ተባባሪነትን ማስተማር?

እምቢኝ ለጎጠኞች! እምቢኝ ለዘረኞችና ለበታኞች!

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በቆራጥ ልጆቿ ትግል ያቸንፋል!

አቶ ሰውየው ከሰሜን አሜሪካ